# በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ቢሮ

## የቁም እንስሳት ግብይት የአገልግሎት ክፍያ መመሪያ

የቁም እንስሳት ግብይት ሥርዓትን ለማስፈፀም በወጣዉ አዋጅ ቁጥር 819/2006፣አዋጁን ለማስፈፀም በወጣዉ ደንብ ቁጥር 341/2007 እና ደንቡን ለማስፈፀም በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ የንግድ ሚኒስቴር ባወጣዉ መመሪያ ቁጥር 004/2007 አንቀጽ 14 ንዑስ ቁጥር(3) መሠረት ይህ መመሪያ ወጥቷል።

### ክፍል አንድ

### ጠቅላላ

1. **አጭር ርዕስ**

ይህ መመሪያ የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት ንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ የቁም እንስሳት ግብይት የአገልግሎት ክፍያ መመሪያ ቁጥር 25/2010 ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. **ትርጓሜ**

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሠጠዉ ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ዉስጥ፣

1. የአገልግሎት ክፊያ ማለት የግብይት ተዋንያኑ በቁም እንስሳት ግብይት ለመሣተፍና በመሣተፍ ላገኙት አገልግሎት የሚፈጽሙት ሕጋዊ ክፍያ ነዉ።
2. አዋጅ ማለት የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 ነዉ።
3. በአዋጁ አንቀጽ 2 የተሠጠዉ ትርጓሜ ለዚህ መመሪያ አፈፃፀም ተፈፃሚነት ይኖረዋል።

3. **የመመሪያዉ ተፈፃሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ በቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አገልግሎት በሚያገኙ ግለሰቦች፣የግል ድርጅቶች፣መንግስታዊና መንግስታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ ይሆናል።

## ክፍል ሁለት

### 4. የማስፈፀሚያ ዝርዝር ታሪፍ

| ተ.ቁ | የገቢ አርዕስት | የክፍያ መጠን በብር |
|---|---|---|
| 1 | የብቃት ማረጋገጫ አዲስ ሲሠጥና ነባር ሲታደስ | |
| | 1.1. አዲስ ብቃት ማረጋገጫ ሲሰጥ | 100 |
| | 1.2. ነባር የብቃት ማረጋገጫ ሲታደስ | 100 |
| 2 | ለመጫኛና ማዉረጃ መደላድል | |
| | 2.1. እንስሳት በተሽከርካሪ ሲጫን | |
| | ለዳልጋ ከብት | 15 |
| | ለጋማ ከብት | 15 |
| | ለበግና ፍየል | 10 |
| | 2.2. እንስሳት ከተሽከርካሪ ሲወርድ | |
| | ለዳልጋ ከብት | 15 |
| | ለጋማ ከብት | 15 |
| | ለበግና ፍየል | 10 |
| 3 | የከብት ገበያ ቀረጥ(ከበረት ሲወጣ) በቁጥር | |
| | ለዳልጋ ከብት በቁጥር | 20 |
| | ለጋማ ከብት በቁጥር | 20 |
| | ለበግና ፍየል በቁጥር | 5 |
| 4 | መሸኛ ለመስጠት | |
| | 4.1. ከገበያ ማዕከል ወደ ቀጣይ መዳረሻ ቦታ ለመሸኘት መሸኛ ለመስጠት በእንስሳት ቁጥር | 10 |
| 5 | ለጤና ምርመራ | |
| | ለዳልጋ ከብት በቁጥር | 15 |
| | ለጋማ ከብት በቁጥር | 15 |
| | ለበግና ፍየል በቁጥር | 10 |

| ተ.ቁ | የገቢ አርዕስት | የክፍያ መጠን በብር |
|---|---|---|
| 6 | ለጆሮ መለያ ቁጥር ሲሰጥ በቁጥር | |
| | ለዳልጋ ከብት በቁጥር | 10 |
| | ለጋማ ከብት በቁጥር | 10 |
| | ለበግና ፍየል በቁጥር | 10 |

## ክፍል ሶስት

### 5. የመተባበር ግዴታ

ማንኛዉም ሰዉ ይህን መመሪያ ለማስፈፀም በሚደረግ ማናቸዉም እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

### 6. መመሪያዉ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በንግድ ኢንዱስትሪና ትራንስፖርት ቢሮ ከፀደቀበት ከሕዳር 06/2010 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

ባበክር ሀሊፋ አብደላ

የቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልላዊ መንግስት

ንግድ ኢንዱስትሪ ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ

ሕዳር 06/2010 ዓ/ም